Flintstone Homes
for you®

# ፍሊንትስቶን

## ኢንጂነሪንግ አክስዮን ማህበር

### የፍሊንትስቶን ሆምስ እናት ኩባንያ

## አዲስ ባለአክሲዮኖችን ለመጋበዝ የወጣ መግለጫ



በአዋጅ 1243/2013 እና 1248/2013 መሰረት የተዘጋጀ

## 1 ስለ ፍሊንትስቶን ኢንጅነሪንግ አ.ማ.

በደረጃ ስምንት ስራ ተቋራጭነት በፀደቀ ይሁኔ ወልዱ በ1984 በመመስረት በመላ ሃገሪቱ የውሃ፣ የመብራት ሃይል፣ በመንገድ፣ በዩኒቨርሲቲ እና በመንግስት የቁጠባ ቤቶች ፕሮጀክቶችን የመሳሰሉ የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን ያከናወነ ሲሆን በአጠቃላይ ከ13 ቢሊዮን ብር የሚያወጡ እና 1.1 ሚሊዮን ካ.ሜ የሚሸፍኑ 95 የግንባታ ፕሮጀክቶችን በማጠናቀቅ በአገሪቱ ግዙፍ አሻራዎችን አኑሯል::

ከኢትዮጵያ ሚሊኒየም ጋር ተያይዞ የመጣውን የግንባታ ዘርፍ መነቃቃት ተከትሎም ፍሊንትስቶን ሆምስ በሚል ስም በማደግ ላይ የነበረውን የሪልስቴት ዘርፍ በመቀላቀል በአጭር ጊዜ የቤት ገበያውን በአርዓያነት መምራት ችሏል። ፍሊንትስቶን ከተቋቋመ ከ24 አመታት በኋላ በ2008 ዓ.ም. ከግል ድርጅትነት ወደ አክሲዮን ኩባንያነት ተሸጋግሯል።

### እሴቶች

- በትብብር ጸጋ የተገራ የፉክክር እልህ
- በፈጠራ ፈርጥ የበለጸገ የትጋት ፍሬ
- በቅንነት ላይ የታነጸ ታማኝነት
- ከሁለገብነት የመነጨ ዘመን ተሻጋሪነት

**የፍሊንትስቶን ራዕይ:**
እያንዳንዱ በገዛ ቤቱ፣ ሁሉም ባማረ ውብ መንደሩ፣


**የፍሊንትስቶን ተልዕኮ:**
የኢትዮጵያን የቤት ገበያ በአርአያነት መምራት

## 2 የተሰማራባቸው ዘርፎች

የፍሊንትስቶን ኢንጂነሪንግ ኩባንያ ዋና መተዳደሪያው እና የተቋቋመበት ዋና አላማ የኮንስትራክሽን እና የሪልስቴት ስራ ዘርፎች ለመሰማራት ነው። በተጨማሪም የውሃ ቁፋሮ ስራ፣ የኮንስትራክሽን ግብአቶች እና ብረታ ብረት ማምረት እና ከራሱ ፍጆታ ሲተርፍ ማከፋፈል፣ የማሽነሪዎች ኪራይ ሌሎችም ከኮንስትራክሽን ጋር የተያያዙ የንግድ ተግባራትን ያከናውናል።

## 3 ድርጅቱ ካፒታሉን ለማሳደግ የተነሳበት አላማ እና የታቀደዉ የካፒታል መጠን

- ፍሊንትስቶን በሚቀጥሉት አምስት (5) አመታት ሰባት ሺህ (7,000) ቤቶችን የመገንባት ዕቅድ ይዟል።
- ይህ ዕቅድ በመንግስትና የግል አጋርነት አሰራር ሞዴልን በመከተል 2,000 ቤቶችን ለመገንባት የመግባቢያ ሰነድ የተፈራረመበትንና እና በነባሩ የቤት ግንባታ ሞዴል በተለያዩ የአዲስ አበባ ክፍለ ከተሞች እና የኢትዮጵያ ክልሎች ለመገንባት ያቀደውን ተጨማሪ 5,000 ቤቶች ያካትታል።
- እነዚህን የመኖሪያ ቤቶች ለመገንባት የሚያስፈልገው የካፒታል መጠን ስድስት ቢሊዮን ብር እንደሆነ ይገመታል። በመሆኑ ከፍሊንትስቶን የፋይናንስ ምንጭ አንድ ቢሊዮን ቀሪውን አምስት ቢሊዮን በካፒታል ማሳደግ ለማሰናዳት ሲል ኩባንያው ለህዝብ አክሲዮን የመሸጥ ውሳኔን አሳልፏል።
- ኩባንያዉ ከአክሲዮን ሽያጭ በተከታታይ ለአምስት ዓመታት በየአመቱ ብር አንድ ቢሊዮን በመሰብሰብ የቤቶቹን ግንባታ ለማፋጠንና ትርፋማነቱንም ለማሳደግ አቅዷል።



## ከአክሲዮን ሽያጩ የሚገኘው ገንዘብ የሚውልባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች፡

- የግንባታ ግብአቶችን ክምችት ማሳደግ
- የኩባንያው የጀመረዉን የግብዐት ምርትና ማኑፋክቸሪንግ ስራ ማስቀጠል (backward integration)
- ነባርና አዲስ የግንባታ ፕሮጀክቶችን በጊዜና በጥራት በማጠናቀቅ ትርፋማነትን መጨመር

# 4 የፍሊንትስቶን የአክሲዮን ሽያጩ ዝርዝር መግለጫ

| ለሽያጭ የቀረቡ አክሲዮኖች መግለጫ | |
|---|---|
| የተፈቀደ ካፒታል | 5 ቢልዮን 400 መቶ ሚሊዮን |
| የተከፈለ ካፒታል | 400 ሚሊዮን |
| የተፈቀዱ አክሲዮኖች ብዛት | 10 ሚልዮን 800 ሺህ |
| የተከፈሉ አክሲዮኖች ብዛት | 800 ሺህ |
| ለገበያ የቀረቡ አክሲዮኖች ብዛት | 10 ሚልዮን |
| የአንድ አክሲዮን የተጻፈ ዋጋ (ፓር ቫልዩ) | 500 (አምስት መቶ) ብር |
| የአንድ አክሲዮን የዋጋ ብልጫ (ፕሪሚየም) | 250 (ሁለት መቶ ሃምሳ) ብር |
| መግዛት የሚቻለው ዝቅተኛ የአክሲዮን ብዛት | 40 (አርባ) |
| መግዛት የሚቻለው ከፍተኛ የአክሲዮን ብዛት | 4000 (አራት ሺህ) |
| አክሲዮኑ ለሽያጭ ክፍት የሚሆንበት ቀን | ሀምሌ 01 / 2015 |
| የአክሲዮኑ ሽያጭ በአሁኑ ፕሪሚየም የሚጠናቀቅበት ቀን | የባለክሲዮኖች ቦርድ በሚወስነው ቀን |

- ከነባር ባለአክሲዮኖች ውጭ በእያንዳንዱ አክሲዮን ግዥ ላይ ተጨማሪ 250 ብር የዋጋ ብልጫ ፕሪሚየም የሚከፈል ይሆናል። ከአክሲዮን ፕሪሚየም የሚገኘው ገቢ በንግድ ህጉ አንቀጽ 435/1 መሰረት መጠባበቂያ አካውንት ውስጥ የሚቀመጥ ሲሆን ኩባንያው/ ፍሊንትስቶን ከአክሲዮን ሽያጭ አስቀድሞ ያለውን የተጣራ እሴት (ዋጋ) የሚያሳይ ይሆናል።

## የአከፋፈል ስነ-ስርአት

- ደንበኞች ሽያጩ በተከናወነ ወቅት የገዙትን አክሲዮኖች ጠቅላላ ዋጋ መክፈል ይጠበቅባቸዋል።
- ደንበኞች እንደገዙት አክሲዮን ብዛት የሚወሰን የአገልግሎት ክፍያን ይከፍላሉ።

# 5 ከፍሊንትስቶን አክሲዮን የመግዛት ጥቅም

- ከ 30 አመታት በላይ በግንባታ እና ተያያዥ ዘርፎች ገበያውን በአርአያነት እየመራ የሚገኝ አንጋፋ እና ስመጥር ድርጅት ባለቤት/ ባለድርሻ መሆን፣
- ፍሊንትስቶን በስራ ላይ ያለ ድርጅት በመሆኑ አክሲዮኖቹ ትርፍ ማስከፈል የሚጀምሩት የአክሲዮን ሽያጩ ከተፈጸመ ቀን ጀምሮ መሆኑ፣
- ደንበኞች በዚህ ግዙፍ ድርጅት ውስጥ በዕውቀት የታነጸ የልህቀት አሻራቸውን በማኖር፣ ድርጅቱን የመምራት እድል ስለሚያገኙ
- የአክሲዮን ገዢዎች ለአክሲዮኑ ያዋሉትን ገንዘብ በቀጣይ ለቤት መግዣነት ማዋል ቢፈልጉ መጠቀም መቻላቸው
- የትኛውንም መጠን የፍሊንትስቶን አክሲዮን የገዙ ደንበኞች የገንዘቡን እንቅስቃሴ እና የአስተዳደራዊ ተሳትፎን ሙሉ በሙሉ የሚያረጋግጡበት ዲጂታል መተግበሪያ መዘጋጀቱ

| | |
|---|---|
| የድርጅቱ ስም | ፍሊንትስቶን ኢንጅነሪንግ አክሲዮን ማህበር |
| የንግድ መጠሪያ | ፍሊንትስቶን ሆምስ |
| የተመሰረተበት አመት | ጥቅምት 12 1984 ዓ.ም. |
| አድራሻ | አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ |
| ዋና መሰሪያ ቤት | ቦሌ ክፍለ ከተማ ቦሌ ሆምሰ፣ ገርጂ፣ ኢ.አ |
| ስልክ | +251 114663629/31/4168977/8188 |
| ዌብሳይት - | www.flintstonehomes.com |

